# በህገ መንግስታዊ መብቶች ሽፋን ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን በሃይል የመናድ ከንቱ ምኞት

ዮናስ 12/31/13

ሰብአዊ መብት ፣ የፕሬስ ነፃነት፣ የተቃውሞ ሰልፍና መሰል መብቶች በርግጥም በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ሊከበሩ የሚገባቸው መብቶች መሆናቸው ግልጽ ነው። በተለይም የሰብአዊ መብት ጉዳይ ከህገመንግስታዊ ዋስትናም ባሻገር ተፈጥሯዊ መብት ከመሆኑ አንፃር ለድርድር የማይቀርብ መሆኑም ላይ ልዩነት የሚኖረው የለም። ያም ሆኖ ግን እንደኛ ባሉና ዴሞክራሲያዊ ስርዓታቸው ገና በለጋ እድሜ ላይ የሚገኙ ሃገራት ላይ ለእነዚህና በተለይም ለሰብአዊ መብቶች ህገመንግስታዊ ዋጋ መስጠት የግድና ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው። ምክንያቱም የዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ምንጭ የሆነውን ህገ መንግስት ለመገርሰስና ለኋልዮሽ ለመጎተት የሚደረግ ሙከራ መከላከል የሚቻለው በራሱ በህገመንግስቱ በመሆኑ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ታዳጊ ዲሞክራሲ ባለባት ሃገራችን እና ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎችን በተመለከተ ግንዛቤው የሌላቸው ዜጎች በሚበዙበት ሁኔታ ውስጥ ይህንኑ ህገመንግስት ሽፋን ያደረጉ ሃይሎች ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ለመቀልበስ የሚያደርጓቸው ሙከራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰባቸው መምጣቱም ሊሰመርበት የሚገባውና የዚህ መጣጥፍም ዋነኛ ጭብጥ ነው። በተለይ በህገመንገስታዊ መብት ሽፋን ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን ለመናድ የሚቃጡ ሙከራዎች በአብዛኛው የፕሬስ ነፃነት፣ የሰብአዊ መብት እና የተቃውሞ ሰልፎች በነጠላ እና የሚበዛውን ጊዜ ደግሞ በአንድነት መነሻ በማድረግ ነውና።

በዚሁ መሰረት እነዚህን በግልም ሆኔ በጋራ ህገመንገስታዊ ድንጋጌዎችን መነሻ አድርገው ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ በማሰብ የሚስነዙ አፍራሽ አመለካከቶችንና የሚስተዋሉ ተግባራትን ህብረተሰቡ በውል ተገንዝቦ በምክንያት

እንዲታገላቸውና እንዲያመክናቸው ማድረግ ተገቢ እንደሆነ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ያምናል።

የፕሬስ ነፃነትን፣ የሰብአዊ መብትንና የተቃውሞ ሰልፎችን የተመለከቱ ህገ መንግስታዊ መብቶችን ማብራራት ሰፊና ጥልቅ ነው። ነገር ግን ከተነሣንበት አጀንዳ ላለመውጣትና ይበልጥ ውስብስብ ላለማድረግ ለርዕሰ ጉዳያችን ማሳያ ለሚሆኑ አስረጂዎች ትኩረት በመስጠት ጉዳዩን በሁለት ከፍለን ማየት የሚመረጥ ይሆናል።

ስለሆነም የኋላውን አይተን ዛሬን ለመመልከትና ለመመዘን ይረዳን ዘንድ ከሰብአዊ መብት፣ ነፃ ፕሬስና የተቃውሞ ሰልፍ አኳያ ከሰሞኑ የወጡ መግለጫዎችን እና ሪፖርቶችን በመጠኑ ቃኝተን ከህገመንግስቱና በተለይም የመግለጫው ባለቤቶች ካቀረቧቸው አስረጂዎች አንፃር ጥሬ ምዘና በማድረግ የመጀመሪያውን ክፍል እናያለን።

በመቀጠል በህገመንገስታዊ መብቶች ሽፋን ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ የተቃጡ ሙከራዎች ተቀጽላ መሆኑን የሚያረጋግጡልንን ማሳያዎች እያነሳን የሙከራዎቹን እንደምታና ማረፊያ ከርዕዮተ አላማዊ እይታና ከቀለም አብዮት ፖለቲካ አንፃር በመፈተሽ እናሟርጋለን።

የሚበዙትና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከላይ በተመለከተው አጀንዳ የተጠመዱና ሰለባ የሆኑ ቢሆንም ለማነሳቸው ነጥቦች የአራት ፓርቲዎች ጥምረት ነኝ የሚለውን መድረክ እንደ ማሳያ ወስጃለሁ። በክፍል ሁለት መጣጥፍ በማነሳው የኋላ ታሪክ ዳሰሳ ላይ መድረክ የተሰኘውና በመድረኩ ውስጥ የሚገኙ ፓርቲዎችን ጨምሮ አመራሮቻቸው የዚህ ተግባር ዋና ተዋናዮች የነበሩ መሆናቸውና ዛሬም በዛው ድርጊት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መሆናቸውን እናያለን።

መድረክ ከሰሞኑ በወጣው መግለጫ ለሶስት ጊዜያት ሰላማዊ ሰልፍ ጠይቆ በመንግስት መከልከሉን፣ የሰላማዊ ተቃውሞን መንገድ መዝጋትና የዜጎችን ህገመንግስታዊ መብቶች ማፈን በአስቸኳይ ሊቆም እንደሚገባና በአሁኑ ጊዜ ሃገሪቱ

እየተዳደረች ያለችው በህገመንግስት ሳይሆን በጫካ ህግ፣ በጉልበትና በመሳሪያ ነው፣ወዘተ የሚል ውንጀላ አሰምቷል።

በተለይ እንደምታውን ወደኋላ የምንመለከተውና ምርጫ በደረሰ ቁጥር በተቃውሞ መንገድ በሊቀመንበርነት የሚመጡት ዶ/ር መራራ ጉዲና መግለጫውን ተንተርሰው በሰጡት አስተያየት |አሁን ያለውን የምርጫ ቦርድ እንደምርጫ ቦርድ አምኖ መቀበል ወንጀል ባይሆንም ሃጥያት ነው´ ብለው |ኢህአዴግ ሙሉ ለሙሉ ሰላማዊ ሰልፍን ከመከልከል በላይ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማፈን የስለላ እና የአፈና ወጥመድ ዘርግቷል´ ማለታቸውን ከተለያዩ ሚዲያዎች ከወጡ ዘገባዎች ተመልክተናል።´

ከሁሉ የሚልቀውና ለተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይ ጥሩ ማሳያ ሊሆን የሚችለው የዶ/ር መራራ አስተያየት ደግሞ |ኢህአዴግ ከምርጫ 97 በኋላ የፖለቲካ መድረኩን በአደገኛ ሁኔታ እያጠበበው ነው ´ በማለት በማስረጃነትም የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ፣ የፀረ ሽብር አዋጅ፣ የበጎ አድራጎት አዋጅና የፓርቲዎች የምዝገባ አዋጅን ስለመጥቀሳቸው ከዘገባዎቹ አይተናል።

ይህ ደግሞ የተቃውሞ ሰልፍን ህገመንግስታዊ መብት  ከለላ በማድረግ ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን በሃይል ለመናድ ሙከራው እየተጧጧፈ ስለመሆኑ የሚያመላክትልኝ ነጥብ ነው። ወደሌላውና በተመሳሳይ ለተመሳሳይ ተግባር ከሰሞኑ የተነሳው አጀንዳ ስንሻገር ደግሞ |ነፃውን ፕሬስ´ በተመለከተ የወጣውን መግለጫ እናገኛለን። የመግለጫው ባለቤቶች |የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ድርጅት ነን´ የሚሉት CPJ እና RSF የተባሉ ተቋማት ሲሆኑ በአፍሪካ በርካታ ጋዜጠኞች በእስር ላይ ከሚገኙባቸው ሃገራት ኢትዮጵያ ሶስተኛ ነች በማለት አገሪቷን የፕሬስ አፈና ሱስ ያለባት ሃገር ያስመሰለ ሪፖርታቸውን ከነዚሁና |ታፍነዋል´ ከተባሉት ጋዜጦች ዘገባ አንብበናል።

በሰብአዊ መብት አቀንቃኝ ስም የተሰለፈውና ከሰው ሃገር ፖለቲካ ገብቶ በመፈተፈት የምናውቀው አምነስቲ ኢንተርናሽናል የተባለው ተቋምም  እንዲሁም

በተመሳሳይ ቀድሞ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ስትቆምር በሰራችው ጥፋትና የህግ ጥሰት ተቀጥታና በይቅርታ መውጣቷን የማንረሳትን ብርቱካን ሚደቅሳ አስተያየት መነሻ በማድረግ "ሃገራችን የሰብአዊ መብት ፀር" መሆኗን የተመለከተ ሪፖርት ከማውጣቱም በላይ ለብርቱካን መፈታት አስተዋጽኦው የራሱ ስለመሆኑና አሁንም እነእስክንድርን ያስፈታ ዘንድ ተማጽኖ እንደቀረበለት የሚያመላክት ሪፖርቱን አንብበናል ።

የእነዚህ መግለጫዎች እንደምታ ምንድ ነው? የሚለውን እና ጥሬ ትርጉም ለመገንዘብ ከተቃውሞ ሰልፍ፣ ከፕሬስ ነፃነት እና ከሰብአዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ህገመንግስታዊ መብቶችን ሽፋን ያደረጉ ያለፉ ሁነቶችን ከፕሬሱ ከተቃውሞው ፖለቲካ መንደርና "ከሰብአዊ መብት ተሟጋች" ተቋማቶች መንደር መጀመሪያ መመልከቱ ተገቢነት ያለውና ጉዳያችንንም ግልጽ የሚያደርግልን የተሻለው አማራጭ ይመስለኛል።

የገበያ አክራሪ ሃይሎች የእነሡን መሻት ያልፈቀደን ሃገር እንዳሻቸው አናውጠው ሥርኣት ሊለውጡ የሚጠቀሙባቸው መንገዶች ሁሉ ዴሞክራሲያዊ የሚመስሉ እና ስለ ዴሞክራሲ በሚዘምሩ ተቋማትና ግለሠቦች አማካኝነት መሆኑ ይታወቃል፡፡ የሠብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ በየሃገራቱ ያሉ አኩራፊ ፖለቲከኞችና ኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲከኞች እንዲሁም ፍርፋሪ ለቃቃሚ የሆኑ ፕሬሶችን ከኒዮሊበራል ሚዲያው ጋር ተመጋግበው እንዲሠሩ ማድረግ ዋነኛ ስልታቸው መሆኑም እንዲሁ ጦሱ የደረሰባቸውና ሙከራውን ያከሸፉ ሃገራትን በማስታወስ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ቀደም ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ይህንን አጀንዳ ለማንሣት የተነሣሁበት ምክንያት ምርጫ 97 እና ምርጫ 2002ን ተከትሎ እነዚህ ሃይሎች በሃገራችን የሞከሩትን እና የከሸፈውን የቀለም አብዮት ዳግም ለመቀስቀስ ማኮብኮባቸውን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች በመታየታቸው ነው፡፡ ሃገራችን በምትከተለው የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በሚከተሉ ሃገራት እንደሚደረገው ሁሉ ሃሣብን በነፃ የመግለፅ፣ የመደራጀት፣

የመሥብሥብ እንዲሁም ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ መብት የተፈቀደና ህገመንግስታዊ ዋስትናም የተሰጠው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ግን ደግሞ ሃሣብን በነፃነት በመግለጽ መብት ሽፋን፣ በመሠብሠብና በመደራጀት መብት ስም፣ በሠላማዊ ሰልፍ ጥላ በመከለል የሚደረግ ማንኛውንም ዓይነት ህገወጥ እንቅስቃሴ የመመከትና በህግ አግባብ እርምጃ የመውሰድ መብት እንዲሁ በስልጣን ላይ ለሚገኘው መንግስት የተሠጠ ሃላፊነትና ይኸውም ሃላፊነት በህገመንግስቱ የተረጋገጠ መሆኑንም ወደዋናው ፍሬ ሃሳባችን ከመሻገራችን በፊት ታሠምሩልኝ ዘንድ እሻለሁ፡፡

ከላይ እንደተጠቆመው ከምርጫ ውጭ የሚደረጉ የሥልጣን መያዣ መንገዶች በተለይም የቀለም አብዮት የሚከናወነው በውጭ በሚገኙ አክራሪ ሃይሎችና አክራሪ ዲያስፖራዎች እና በሃገር ውስጥ በሚገኙ የከሠሩ ፖለቲከኞች፣ ፓርቲዎቻቸውና አንዳንድ ፕሬሦች ነው፡፡ በተለይ ብዙ ሃይማኖቶችና ብሄር ብሔረሰቦች ባሉባቸው ሃገራት ላይ በሃይማኖት ሽፋንና በብሔር ስም የሚደረጉ የአክራሪ ሃይሎችን ግርግሮች ለቀለም አብዮት መቆስቆሻነት እንደ ሁነኛ መሣሪያ አድርገው ሊጠቀሙባቸው ይሞክራሉ፡፡ በሠላማዊ ሠልፍ ስምና በሃይማኖት ሽፋን ሲደረጉ የነበሩ ግርግሮችና ሁሉ በ97 እና 2002 የከሸፈውን የቀለም አብዮት የሚያስታውሡ ናቸው።

ይህን በተገቢው ሁኔታ ግልጽ ለማድረግና ለማብራራት ደግሞ ወደ 97ቱ እና 2002ቱ ምርጫና ምርጫውን ታከው ወደተደረጉ የቀለም አብዮት ሙከራዎች ማምራትና አስተሳስሮ ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ በአንድ አገር ውስጥ የቀለም አብዮት እንዲኖርና አልፎ ተርፎም እንዲሳካ ከማድረግ አኳያ ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ ጠንካራ አንድነት ያለው የተቃዋሚ ጎራ መኖር እንዳለበት "የተራቀቁት" የቀለም አብዮተኞች ይገልፃሉ፡፡ በአገራችንም በ97 ዓ.ም ተሞክሮ የከሸፈው የቀለም አብዮት የተለያዩ ነገር ግን ከሞላ ጎደል በአንድ ተመሳሳይ የቀለም አብዮት ስትራተጅ የሚመሩ ተቃዋሚ ድርጅቶች የመሩትና የተወኑበት ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ጀምሮት በሂደት ቅንጅት ከተፈጠረ በኋላ መሪነቱን

የተቆጣጠረው የ97ቱ የከሸፈ ሙከራ ከሞላ ጎደል በሁሉም ተቃዋሚዎች የታመነበትና የተደገፈ የቀለም አብዮት ጥንስስ ነበር፡፡

በአገራችን የሚገኘው የተቃውሞ ጎራ ምንም እንኳን ባነገበው አላማና በኪራይ ሰብሳቢ ባህሪው አንድ ቢሆንም ከምርጫ 97 በኋላ የአገሪቱን ህጎች አክብሮ ለመታገል ዝግጁ በመሆንና ባለመሆን መካከል ልዩነቶች እያሳየ መጥቷል፡፡ በዚህ መሠረት አንዳንዶቹ በተለይም ኢዴፓ የጨዋታውን ህግ አክብረው ለመንቀሳቀስ ዝግጁነት ያላቸው ይመስላል። ገገርው ፓርቲ ከ98 ዓ.ም ጀምሮ በከፈታቸው ልዩ ልዩ የድርድር መድረኮች በመሳተፍ ሂደቱን በሚጠቅማቸው ወይም የጋራ ጥቅሞችን በሚያረጋግጥ አኳኋን ለመቃኘት ዝግጁ መሆናቸውን ማሳየት የጀመሩ ፓርቲዎች አሉ፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች የምርጫ ህጉን በማሻሻልና የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡን ተደራድረው እስከማጽደቅ፤ በእርሱም እስከመመራት የደረሰ ተሳትፎ አሳይተዋል፡፡

ምንም እንኳን እነዚህ የተቃዋሚ ክፍሎችም ሂደቱን የሚያጥላላ ዘመቻ ከማድረግ አኳያ ያልተሻገሩት ወንዝ ያለ ቢሆንም ደፍረው የፀረ ህገ-መንግስት ቅስቀሳና የአመፅ ጥሪ ማካሄድ ውስጥ ባለመግባት ከፅንፈኛው የተቃዋሚ ጎራ የተለየ አካሄድ መከተል እንደሚፈልጉ አመላክተዋል፡፡ ይህ አዝማሚያ በአምስተኛው አገራዊ ምርጫ ሂደት የአመፅ ሃይሎች በሚወስዱት አቋም ወይም መዋለል የሚፈተን ቢሆንም ሰሞኑን በሰላማዊ ሰልፍ ስም እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴና የመግለጫ ጋጋታ በህገ መንግስቱ ሽፋን ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በሃይል ለመናድ የወለም ዘለም አካሄድ እየታዬ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

ፅንፈኛ ተቃዋሚው ከ97ቱ እና ከ2002ቱ ስህተት ካለመማሩም በላይ የለየለት ኪራይ ሰብሳቢ ፍላጎቱን ለማሳካት አመፅን ጨምሮ በማንኛውም መንገድ ስልጣን ላይ መውጣት የሚሻ ኃይል ነው፡፡ ለዚህም ሲል ችግር በሌለበት ችግር የተፈጠረ አስመስሎ ሰፊ የፈጠራ ውዥንብር ይነዛል፡፡ ዴሞክራሲያችን ለጋ ከመሆኑ በመነሳት ዴሞክራሲያዊ ስርአቱን ለመገንባት ከሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ሾልከው የሚፈፀሙ አንዳንድ ግለሰባዊ የስነ-ምግባር ጥሰቶችን አጋኖና አባዝቶ

በማቅረብ ህዝቡ በስርአቱ ላይ አመኔታ እንዲያጣ ለማድረግ ሌት ተቀን በመፍጨርጨር ላይ ይገኛሉ፡፡ በገዢው ፓርቲና በመንግስት በኩል ስህተት ከታጣም በአንድ በኩል ሆን ብሎ ህግ በመጣስ በመድበለ ፓርቲ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደቱ ላይ ፈተና እየደቀነ መንግሥት ህግ ለማስከበር ሲንቀሳቀስ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠበበ እያሉ ይቀሰቅሳሉ፤ በሌላ በኩል መንግስት ዴሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ ምህዳሩ ጠቧል የሚል ወቀሳ እንዳይቀርብ በመስጋት የህግ ጥሰትን አይቶ እንዳላየ ሲያልፍ ደግሞ ህግ የመጣስ መንፈስ እንዲበራከትና ወደ አመፅ ለመንደርደር የሚያመች ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል እንቅስቃሴ ያካሂዳሉ፡፡

በተጨማሪም ከዓለም አቀፍ የቀለም አብዮት ሃይሎች ጋር በፈጠሩት ተመጋጋቢ ግንኙነት ስርአቱን ጥላሸት የመቀባት ሰፊ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻን በማካሄድ ላይ ናቸው፡፡

በቅርቡ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎችን እንደ አባሎቻቸው በማቅረብ ግፍ የተፈፀመ አስመስሎ ማቅረብ፣ በደረቅ ወንጀል የታሰሩ ሰዎችን ስም ለቃቅሞ በፖለቲካ የታሰሩ አስመስሎ ተደጋጋሚ የፕሬስ መግለጫ ማውጣት፣ በሚዲያ በሚካሄዱ ውይይቶችና በፕሬስ ውጤቶች በአምደኝነት ስም በሚለቋቸው ፅሁፎች ላይ ብጥብጥና ሁከት ቀስቃሽ መልዕክቶችንና ሃሰተኛ ውንጀላዎችን በማሰማትና በመጨረሻም ድርጊታቸው የሕግ ተጠያቂነት ሲያስነሳባቸው "የመጻፍ መብታችን ተጣሰ" ብሎ ዘመቻ መክፈት የተለመዱ ክስተቶች ሆነዋል፡፡

ፅንፈኛው የተቃዋሚ ሃይል ለቀለም አብዮቱ መደላደል ሆኖ የሚያገለግል ቅሬታ በህዝብ ዘንድ ለማሳደር ሰፊ ጥረት ቢያደርግም ህዝቡ ሂደቱን በቅርብ እየተከታተለ ይገኛል፡፡ ሂደቱን ከመሰረታዊ ጉዳዮች በመነሳትና በመመዘን በአገራችን የለውጥ ጉዞ እርካታ ሊያገኝ በመቻሉ የቀለም አብዮት መሳሪያ የሚሆንበት እድል ከቶውንም ሊከሰት አልቻለም፡፡ ከዚህም አልፎ በአገራችን በአጠቃላይ ባለፉት 22 ዓመታት የተፈጠረውን መልካም እድል ሁሉ ታሳቢ በማድረግ ከዚህ የሚያናጥበው አንዳችም አይነት ሁከት ወይም ግርግር እንዳይኖር ፍላጎቱን በይፋ አሳይቷል፣እያሳዬም ይገኛል፡፡

የዘንድሮው የፅንፈኞች ሙከራ ከ97 የከሸፈ አብዮት በባሰ ሁኔታ  ከተስፋ መቁረጥ በመነሳት የሚያሰሙት ማላዘን ይህን በተጨባጭ ያመላክታል፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀረ እድል ቢኖር አንዳንድ ሁኔታዎችን፣ክስተቶችን፣ስፍራዎችንና ወቅቶችን ጠብቀው ከሕግ አግባብ ውጭ  የተቃውሞ ሰልፍ ካላደረግን ብሎ የመግለጫ ጋጋታ ማውጣት ነው ፤ ይህም ላቀዱት የቀለም አብዮት ማስፈጸሚያ እንደ አንደኛው ስልት ሊጠቀሙበት ያሰቡ ለመሆኑ አንዱ ግልጽ ማሳያ ነው። የዚህን እኩይ ተግባር መዳረሻ በተመለከተም  ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር ይዘን በተከታዩ መጣጥፍ እንገናኛለን፡፡